# የብርቱኳን ሚደቅሳ እስራትና የሰላማዊው ትግል እንቅስቃሴ ጥያቄ

ለኣከ ገ/ፃድቅ
ጥር 4 2001 ዓ ም

የኣንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ድርጅት መሪ የብርትኳን ሚደቅሳ እንደገና መታሰር ኣገሪቱ ከ1997ቱ የምርጫ ኣዙሪት ለመውጣት ኣለመቻልዋን የሚያስገነዝብ ክስተት ነው።

የብርትኳን እስራት በተለያዩ ምሁራን ከተሰጠው የህጋዊነት ትንተና ባሻገር ብዙ ጥያቄዎችን ያስነሳል። ጥያቄዎችን ከመመልከት በፊት በብርቱካን እስራት ዙርያ ያሉ ሁኔታዎች መዳሰስ ልሞክር። ከዛም ቀጥሎ ሰላማዊ ዲሞክራስያዊ ትግል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዘላቂ ሰላም የሚያስገኝ ምንም ኣማራጭ የሌለው መንገድ መሆኑ የመከራከርያ ነጥቦችን እግረመንገዴን ኣነሳለሁ።

የኢህወደግ መንግሥት ቀድሞ ቅንጅት ተብሎ ከሚታወቀው ተነጥሎ የወጣው የኣንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ድርጅት ሲቋቋም ህጋዊ እውቅናውን ከማጓተትና ከማስተጓጎል በቀር፣ ህጋዊነት ካገኘ በኋላ ግን ሊገታው የማይችል የፖለቲካ ሃይል መሆኑ ተገንዝቦኣል። በብርቱካን የሚመራው ድርጅት እነ ሀይሉ ሻውል ከመሳሰሉ ኣደገኛና ከፋፋይ መሪዎች ይዘዋቸው ከወደቁ ድርጅቶች ራሱን በመለየት የተሻለ የፖለቲካ ራእይ ወዳለው ደረጃ ማሸጋገር በቅቶኣል። የ1997ቱ የምርጫ ሁኔታም በ2010 ዓ ም እንደሚደግም እስካሁን ያሳየው እንቅስቃሴ ያመለክታል። የኢህወደግ ጥረትም ማንኛውንም ዋጋ በመክፈል ይህን ስጋት ማስወገድ ነው።

ብርትኳን ሚደቅሳ የታሰረችበት ሁኔታ ስናይ በኢህወደግ ስርዓት የረቀቀው በኣገሪቱ ህገመንግሥት ያሉ የሰብኣዊ መብት ኣንቀፆችን ቃል በቃል የሚጥስ ነው። በምዕራፍ ሦስት ክፍል ኣንድ፣ በኣንቀፅ 16 በ "ኣካል ደህንነት" ርእስ ስር፣ “ማንኛውም ሰው በኣካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት ኣለው” የሚል ሰፍሮኣል። ኣንቀፅ 17 ቁጥር 2ትም፣ “ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ሊያዝ፣ ክስ ሳይቀርበበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር ኣይችልም” ይላል። የታሰረችበት ሁኔታ ግን ክስ ሳይመሰረትባት በደህንነት ሰዎች ድንገተኛ ወከባና ግፍተራ፣ በሌሎች ሰዎችም ድብደባ የታከለበት መኖሩ ይገለፃል። በተለይም ኣስነዋሪና መወገዝ ያለበት ወንጀል በፕሮፌሰር ተኮላ ዕሁፍ ላይ የተጠቀሰው በድብቅ ቪድዮ በማንሳት ስምዋን የማጉደፍ ኣሳፋሪ ተግባር ነው። የኢህወደግ መንግስት ከነእንግሊዝና ኣመሪካ የስለላ ወኪሎች የሚያገኘው የብዙ ወጪ ስልጠናም የሰላማዊ ዜጎችን መሠረታዊ መብት በመድፈርና መርገጥ ተግባር ላይ እንደሚያውል ነው።

ብርቱኳን የታሰረችበት ምክንያትም ከእስርቤት የተለቀቀችበት ምህረት በኣገሪቱ ህግ መሠረት በፕረዚዳንቱ ሳይነሳ መሆኑን እራስዋ በሰጠችው የማብራርያ ቃል

በ www.kinijitethiopia.org/docs/UDJ/articles/birtukan_WORDS.pdf) ይገኛል። የመንግስት አፈቀላጤ አይጋ ፎረም በታሰረች ማግስት "ብርትኳን ምህረትዋ ተነጠቀች ወዘተ" በማለት አትቶ ነበር። ክሱም የጅምላ ውንጀላና መንግሥትን የሚዳፈሩ ተቃዋሚዎችም ለመጪው አጋጣሚ ለእስር ለመዳረግ በሩን ገርበብ አድርጎ የተወ መኖሩን ያመለክታል። የኢህወደግ መንግስት ቀድሞዉንም ቢሆን በተቃዋሚ መሪዎች ክስ ሲመሰርት ፖለቲካ ስልጣኑን ከማስጠበቅ የተለየ ዓላማ ስለሌለው የብሄረሰብ ግጭት ለመቀስቀስ ተሰማሩ ያላቸውን ግለሰቦች የማጣራት ፍላጎት አልነበረውም። በብሄረሰብ ግጭት ቅስቀሳ ራሱም ጭምር ተጠያቂ ነውና።

የሚገርመው ነገር የተቃዋሚ መሪዋን እድሜ ልክ ትታሰራለች ብሎ ሲያውጅ የራሱን እድሜ ዛሬም ታብቃ ነገ ተማምኖ ማደር የማይችል መንግሥት መሆኑ ነው። የመለስ ዜናዊ የኢህወደግ መንግሥት ልክ እንደ ፋሺስቱ የመንግሥቱ ሓይለማርያም ደርግ ምንኛ ድንቁርና የተጫነው ትእቢት እንዳለው ያሳያል። እንደሚለው ከሆነ ታሳሪቱን ለመፍታት ሲገደድ በዚህ ምክንያት የምትፈታበትን የመውጫ በር ጨርሶ ዘግቶታል ማለት ነው። ሆኖም ግን ለወደፊቱ ርካሽ መፍትሄ እንደሚሻና አመካኝቶ እንደሚለቃት የምናየው ይሆናል።

የአንድነት መሪዋን እንደ አዲስ ባገረሽ ክስ ሰትታሰር የሚያስነሳው መሠረታዊ ጥያቄ አለ፤ ይኸውም ወደ ኋላ ስንመለከት፣ የምህረቱ የሽምግልና ተውኔት የአፈፃፀም ትልቅ ስህተት የነበረበት መሆኑ ነው፡፡ ዋናው ስህተት የመነጨውም ከተቃዋሚ መሪዎች ራሳቸው መሆኑ "ሃቅን ፍፁም ለመሸምጠጥ..." በሚል ብርሃኑ ነጋ፣ ሙሉነህ እዩኤልና አንተነህ ሙሉጌታ (በግንቦት ሰባት ድረገፅ) ከፃፉት ምስክርነት በቁጥር "2ረ" ስምንተኛ ነጥብ ላይ "... ሽማግሌዎቹ እናንተ ይቅርታ የምትጠይቁት በሽማግሌዎቹ በኩል ለኢትዮጵያ ህዝብ ነው። ይህንን ደብዳቤ ከኛ በቀር ማንም አያየውም።...." እንዳሉዋቸውና እንዳመኑዋቸው ያትታሉ።

ተቃዋሚ መሪዎች ሲፈቱ ኢህወደግ ወዶ ሳይሆን በውጭና በኢትዮጵያ ህዝብ ተቃውሞ ግፊት ተገዶ መሆኑ እያወቁ ፈር ባለው መንገድ እንኳ መደራደር አልቻሉም ነበር። ከመታሰራቸው በፊትም ጀምሮ የነበራቸው የህዝባዊ ሓይል ድጋፍ እንዴት በከንቱ እንዳባከኑና የሰላማዊ የፖለቲካው እንቅስቃሴ ትግል እንዳኮላሹት ከዚሁ መረዳት ይቻላል። ለአብነት ያህል ገና ሳይታሰሩ የጀመሩት ወደ ሥልጣን የመቆናጠጥ ድርድር የጥቅምቱን የሰላማዊ ሰልፍ ጥሪ በመሰረዝና የህዝባዊ ሓይል ደጀን ከንቱ በማሰቀረት ከመንግሥት ጋር በከፍተኛ ምስጢር ከህዝብ ተደብቀው ለመደራደር ሲሞክሩ በመጨረሻ ለእስር በቅተዋል። የፖለቲካ ትግል ራእያቸው ከምርጫ ማግስት የማያልፍና እምነታቸው በህዝብ ድጋፍ ደጀንነት ሳይሆን በመሰሪነቱ የታወቀው መንግሥት የመደራደር ቀናነት ላይ ነበር። ከዛ ሁሉ ውድቀትና ኪሳራ በኋላ ብርቱኳን እንደገና አሁን ስትታሰር የትጥቅ ትግል ደጋፊዎች "ሰላማዊ ትግል እኮ ድሮዉንም አይሰራም" በማለት መታሰርዋን ለያዙት የትጥቅ ትግል አቋም ድጋፍ እንደ ማረጋገጫ መጠቀም ጀምረዋል።

ሌላው የብርቱካን እስራት የሚያሰነሳው ጥያቄ የሰላማዊው ዲሞክራስያዊው ትግል እንዴት ይቀጥል የሚል ነው። የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ድርጅት የሚከተለው የሰላማዊ ትግል ዓላማ የብርቱኳን መታሰር ፈተና ውስጥ መክተቱ

ግልፅ ነው። ድርጅቱ ያቆጠቆጠበት ጊዜ ኣጭር ከመሆኑም በላይ የሰላማዊዉን ትግል ሂደት በምን ዘይቤዎች እንደሚመራ በትምህርትም ወይም በህዝባዊ ተሳትፎ ትግል ያስመሰከረበት መድረክ ወይም ልምድ የለም። የታሰረችበት ምክንያት እንኳ ብንመለከት፣ የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ በሚል ወይም የኢትዮጵያ መሬት ለሱዳን ገምሶ የመስጠት ክህደት ተቃውሞና በመሳሰሉ ኣበይት ጉዳዮች ኣንስታና ህዝብ ኣስከትላ መስቀል ኣደባባይ ስትወርድ ኣይደለም።

ከፖለቲካ እስረኞች ነፃነት ጥያቄ ጋር በተያያዘ የሰላማዊው ትግል ኣካሄድ መላ ያልተከተለ መሆኑ ኣንድ ምሳሌ ላቅርብና፣ ብርቱኳን ተዱ ኣፍሮ የሚባል ዘፋኝ ለመጠየቅ እቅፍ ኣበባ ይዛ ወህኒ ቤት ወርዳ እንደ ነበር ይነገራል። ከዚህ መገንዘብ የሚገባ ነገር ቢኖር ተዱ ኣፍሮ የህሊና እስረኞች ትክክለኛና ኣይነተኛ ኣብነት ተደርጎ መወሰድ ያለበት ነው ወይ የሚል ጉዳይ ያስነሳል። በኔ ኣመለካከት ኣካሄድዋ በኣንድ ግለሰብ ብቻ ላይ ያተኮረ የፖለቲካ ድጋፍ ለማግኘት የታሰበ ዘላቂነት የሌለው ቁንፅል ኣስተሳሰብ በመሆኑ የእስረኞች መፈታት ጥያቄ የሚወክል ኣብነታዊ እንቅስቃሴ ኣይደለም። የተቃዋሚ መሪዎችን ያስፈታው ሽማግሌ የጀመረው የሁሉም ፖለቲካ እስረኞች መፈታት ጥረት በብርቱኳንና ድርጅትዋ እንደ ኣንድ የትግል ዓላማቸው ኣንስተው መታገል የነበረባቸው ይመስለኛል። ኢህወደግ ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ ስማቸው ተቀብሮ በእስርቤት ለኣመታት እየማቀቁ ያሉ በኣስር ሺዎች የሚቆጠሩ የሂሊና እስረኞች በኣገሪቱ ኣራት ማእዘኖች እንደሚገኙ ሁላችንም እናውቀዋለን። ይህ ባለመሆኑም የብርቱኳን መታሰር ራሱ በሰላማዊው የትግል ሂደት ላይ ሕዝብ ሊከተለው የሚችል የራሱ የሆነ ፈለግ ይታይበታል ብሎ መናገር ያስቸግራል። በሰላማዊ ትግል ሂደት ሊዘከር የሚችል የኣመራር ትእምርት (symbolism) መፍጠር ራሱን የቻለ ሓይለኛ የትግል መሣርያ ነውና።

ተቃውሞን የማደራጀት ኣስቸጋሪነት ባለው የሰብኣዊ መብት ረገጣ ምክንያት ኣዳጋች መሆኑ ቢታወቅም የማይቻል ግን ኣይደልም። ሰላማዊ ሰልፍም የሚወጣው በኢህወደግ የፈቃድ ወረቀት ብቻ የሚወሰን ከሆነ ትግል ሊባልም ኣይገባም። እንደገና የመታሰርዋ ሁኔታ በምንም ምክንያት ይሁን በምን የማይቀር እንደነበር ግልፅ ነበር፤ ድርጅትዋም ከስዋ በኋላ ትግሉ እንዴት እንደሚቀጥልበትና እስዋን ለማስፈታት ምን ኣይነት የሰላማዊ ትግል ስልቶች እንደሚከተል ግን ካሁኑ መተንበይ ባያዳግትም ገና የምናየው ይሆናል።

ቅንጅት እንደተበተነ የቀድሞ መሪዎቹ የየራሳቸው የትግል ፈርጅ ይዘው ተለያየተዋል። ከነሱም የግንቦት ሰባት ድርጅት ህቡእ የትጥቅ ትግል መምረጡም ኣስታውቆኣል። ሰላማዊ የዲሞክራሲ ትግል ህዝብ መሪዎቹን በመከተል መተግበርና መዳበር ያለበት ባህል ነው። ለዚህም ነው ይህን ተለምዶ እውን የሚያደርግና በሕገመንግሥቱ የሰፈሩ መብቶች እንዲጠበቁ ኢህወደግን የሚያስገድድ የተቃውሞ አመራር በመታጣቱ ብዙዎች የትጥቁ ትግል ኣማራጭ እንደሌለው የሚከራከሩት።

በብሄረሰባዊ ውንጀላ "ወያኔ" ብለው መጥራትን የሚወዱት የኢህወደግ መንግሥት ወንጀል በፈፀመ ቁጥር ወደ ትጥቅ ትግል እየገፋፉን ነው በማለት እርስ-በእርስ ጦርነት ሊያስከትለው የሚችል ችግር ያስጠነቅቃሉ። የኢህወደግ ወንጀል በጨመረ

ቁጥር ሕዝቡን ከማስተባበር ይልቅ ሰላማዊ ትግልን ውድቅ በማድረግ የትጥቅ ትግልን እንደ ትክክለኛና ኣማራጭ የታጣበት እርምጃ መውሰድ የተዛባ ኣስተሳሰብና የስህተት እርምጃ ነው። ዋናው ችግር ምክክራቸው ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ከማድረግ ይልቅ እሮሮኣቸው በየኢህወደግ መንግሥት ላይ ብቻ ያተኮረ በመሆኑ ነው።

የትጥቅ ትግል ደጋፊዎች ምንጊዜም ቢሆን ሊመልሱት የምይችሉት ጥያቄ የሥልጣን ንጥቅያው ውጤት ዲሞክራስያዊ እንደሚሆን ዋስትና ወይም ማረጋገጫ ሊሰጡበት ኣይችሉም። በጉልበት የሚመጣው ታጣቂ ሓይል እንደ ኢህወደግ ሆኖ የሚገኝበት ወሳኝ ዕድል ስላለው ስልጣኑን እንዴት ወደ ሕዝብ እጅ ሊገባ ይችላል ለሚለው ጥያቄ ራሱን በራሱ የሚመልስ ማለቅያ የሌለው የጦርነት ኣዙሪት ውስጥ የሚያስገባ ነው። የትጥቅ ትግል፣ ለሰላማዊ ትግል እጅግ ተፈላጊ የሆነውን የሚከተለው የዲሞክራስያዊ ስርዓት ምስረታ ባህላዊ ግንባታ የሚንድ ፅንሰ ሃሳቡንም ከወዲሁ የሚቀጭ ኣመፀኛ እርምጃ ነው። የህወሓት የትጥቅ ትግል ከዚሁ የሚለይ ኣልነበረም፤ ሰላማዊ ተቃዋሚዎቹን እያጠፋ የመጣ በኣፈሙዝ የሚያምን ድርጅት ነው። ለሥልጣን ያበቁት ጀግና ታጋዮችና ዋና ባለሥልጣናት እንኳ ለሂወታቸው ዋስትና ሊያገኙበት ኣልቻሉም። ሌላ ቀርቶ የኣገር ክህደትም ተፈፅሞበታል። ከኢህወደግ በኋላ እሱን ለማጥፋት የተፈጠሩ የደቡብ፣ የምሥራቅም ሆኑ የመሃል ኣገር ነፍጠኛ ተቃዋሚዎችም ጠላት ከሆነው ከኤርትራ መንግሥት ጋር በመዶለት ኢህወደግን ለማጥፋት በሚል ሰበብ በኢትዮጵያ ላይ ክህደት ሲፈፅሙ ቆይተዋል። እውነት የኤርትራ መንግሥት ጦርነት በማካሄድ በኢትዮጵያ ዲሞክራስያዊ መንግሥት ለመመሥረት ተቃዋሚዎችን ይረዳል ብሎ የሚያስብ ጤነኛ ኣእምሮ ሰው ኣለ?

የትጥቅ ትግል ደጋፊዎች እንቅስቃሴው እንደ ኢህኣፓ የከተማ ደፈጣ፣ መፈንቅለ መንግሥትና እንደ ኢህወደግም የበረሃ ሽምቅ ውግያ ስልቶች፡ የትኛውን እንደሚከተሉ ግልፅ ያረጉት ነገር ባይኖርም ተዋጊ ሃይልን ለማደራጀት የሚፈጀው ገንዘብና ኣመታት ከሚከፈለው መስዋእትነት ጋር እንኳን ቢሰላ ኣንድ ኣሳማኝ ነጥብ የላቸውም። የትጥቅ ትግል በደርግ ጊዜ ያለቀው ወታደርና ሰላማዊ ህዝብ እንዲሁም የወደመ ንብረት በተለይም ደግሞ ያስከተለው የብሄረሰቦች ከፋፋይ ፖለቲካ እንደ ኣዲስ የሚደግም የጥፋት ሂደት ነው። ወደ ቂም በቀል ውግያም ሊያመራ ስለሚችል የኣገሪቱን መፈራረስ ምክንያት ሊፈጥርም ይችላል።

በተለይም የኢትዮጵያን ደሕንነት ያሳሰባቸው የትጥቅ ትግል ደጋፊዎችና በኣክራሪ ብሔርተኞች መሓከል ያለው የትጥቅ ትግል ዓላማ ኣምሳያነት ችላ የሚባል ኣይደለም። እነዚህ ሁለት የተለያዩ ሓይሎች እንዴት መለየትና የማይፈለገውን ከትግሉ ማግለል ይቻላል? የህወሓት ኣንዱ ችግር ይኸው ነበር። ብዙሓኑ ኣገር ወዳድ ኣርበኞች ኣክራሪና ከፋፋይ ግለሰቦች ጋር ኣብሮ በመጓዝ ለሥልጣን ኣብቅቶዋቸዋል። የቅንጅት ኣመራርም ይኸው ተመሳሳይ ችግር ነበረበት።

ለማጠቃለል ያህል የመወያያ ነጥቦችን ኣስፍሬ ልለፍ። በዚሁ በትጥቅና በሰላማዊ ትግል ንትርክ መሃል ለዲሞክራስያዊ ትግል እንቅስቃሴ ዋና ደንቃራ የሆነው

ይኸው የብሄረሰብ ከፋፋይ ፖለቲካ ነው፤ የኢህወደግ በሥልጣን መቀጠል ወሳኝ ምክንያትም ይኸው ብቻ ነው።

ከዚሁ ጋር ብዙ ጊዜ በጥላቻ የፕሮፓጋንዳ ፖለቲካም ይሁን በሌላ የሚነሳ ጉዳይ ላቅርብ፤ ባለፈው ትግራይ "ከኢትዮጵያ በተዘረፈ ንብረትና ሓብት ልታዘቅጥ ነው" ከሚለው የጥላቻ ፖለቲካ ተሻሽሎ በአሁኑ ጊዜ የትግራይ ሕዝብ መታገል ኣለበት የሚሉ ወገኖች ተበራክተዋል። የብሄረሰብ ከፋፋይ ፖለቲካ ኣብቅቶለታል እንዳይባል ከፋፋይ ፖለቲካን በማውገዝ ለሰላማዊው ዲሞክራስያዊ ትግል ኣሰተዋፅኦ የሚያደርጉ ግለሰቦችም ይሁኑ ድርጅቶች ኣልታዩም። ለምንስ የትግራይ ህዝብ? ከማን ጋርና በየትኛው የትግል መድረክ ብሎ የሚጠይቅ ሰውም መኖር ኣለበት። "የትግራይ ህዝብ" በዚህ መሃል ሲነሳ የብሄረሰብ ከፋፋይ ዝንባሌና ኣመለካከት ላይ የተመሠረተ መሆኑ የሚያመለክቱ መነሻዎች ኣሉት። ሥልጣን ላይ ያለው ቡድን መሠረቱ ከትግራይ በመሆኑና የትግራይ ህዝብም በሁሉም ነገር በኣብላጫነት ተጠቃሚ ስለሆነ ኢህወደግን ከሥልጣን መንቀል ፍላጎት የለውም ከሚል የተሳሳተ ኣስተሳሰብ የመነጨ ነው። በተለይ ኣክራሪ ብሄርተኞች እውነቱን እያወቁ የጥላቻውን ዘመቻ በማፋፋም የቂምበቀል ስራቸውን የሚፈፅሙበት እድል ለኣመታት ሲጠባበቁ ቆይተዋል። የ1997ቱ ምርጫ ውጤት ወደዚሁ ኣገር የማውደም እንቅስቃሴ ማምራት ጀምሮ እንደ ነበር ኣይተነዋል። እስከ ኣሁን ድረስ በየቡና ቤቱና ሆቴሉ ፀረ-ትግራይ የጥላቻ ፅሁፎች (Graffiti) በግድግዳ ተጫጭረው ይገኛሉ።

በእርግጥ መረዳት ለሚፈልጉት ወገኖች ፍላጎትና ጥረትም የሚጠይቅ ሲሆን፣ ኣንዳንድ እውነታዎችን ላንሳ፤ ኢህወደግ እንደሚታወቀው በፐሮፓጋንዳ መሰራጫዎቹ ብዙ ልማቶች እየተካሄዱ ነው እያለ በየጊዜው በተለቪዥን ማሳየት ቢሞክርም ትግራይ በኢኮኖሚ እድገት ካዘቀጡ ኣካባቢዎች ከኣፋር ቀጥሎ በሁለተኛነት የምትፈረጅ ናት። ለዚሁም ምክንያት የሚሆኑት የኤርትራው የድንበር ጦርነት ፍጥጫ በኢኮኖሚ እድገትና በግል መዋእለ ንዋይ እድገት ላይ የፈጠረው የማይቻል ሁኔታ፤ በድንበሩ ጦርነት ምክንያት የንግድ መስመሮች ወይም ኣውታሮች በተለይም ከምስራቅና ሰምየን ኣቅጣጫዎች መዘጋታቸው፤ ከደቡብ ወይም ከመሃል ኣገር ያለው የኢኮኖሚ ግኑኝነት ደግሞ በርቀትና በልማት ኣውታሮች ኋላ ቀርነት ምክንያት የሚፈለገው ውህደት ባለመኖሩ፤ ለምሳሌ ከመሓል ኣገር ወደ ሰምየን ከጣልያን ጊዜ ጀምሮ የተመሠረተው የኣውራጎዳና ዋና የንግድ መስመር ተቀልብሶ የንግድ እንቅስቃሴው ኣሁን ከኣዲስ ኣበባ ወደ ባህር ዳር በመደረጉ፤ ለውጭ ንግድ እንቅስቃሴ የሚፈለገው መሥመርና በቅርብ የሚገኘው ወደብ በኤርትራ በመያዙ፤ የኢኮኖሚው ዋና ዋና ክፍሎችና የመንግሥት ኣስተዳደር ለህወሓት ቁንጮ ባለሥልጣናት የቅርብ ኣገልጋዮች በሆኑ ግለሰቦችና ካድሬዎች ሙሉ ቁጥጥር ሥር በመሆናቸው፣ ሌሎች ብዙ ምክንያቶች መጥቀስ ይቻላል። ከዚህም የተነሳ የትግራይ ክልል መንግሥት የክልሉ ተወላጅና የውጭ ባለ ሓብቶችን ለመሳብ የሚያደርጋቸው ጥረቶች ዋጋ ሊኖራቸው ኣልቻሉም። ህወሓት በኢፈርት ኣመካኝነት ቀደም ብሎ ካቋቋማቸው ፋብሪካዎች በቀር የግል ሃብት ተቋማት እንደ ሌላው የኢትዮጵያ ክፍሎች ሊበራከቱ ኣልቻሉም። በተለይም ደግሞ ከደርጉ የእልቂት ዘመናት በኋላ ብዙም ፋታ ሳያገኝ የትግራይ ህዝብ ከኤርትራ ጋር ባለው ጦርነት ተወጥሮ ያለና የኣብዛኛው ነዋሪ ህዝብ ቤተሰብ ኣባላት በዚሁ

የመከላከያ ጦርነት የተሰማራ ነው። እነኝህና ሌሎች ችግሮች በክፍለ ሃገሩ ካደረሱት ጉዳቶች ከፍተኛ የሰው ሓይል እጥረት፣ የኤርትራው ጦርነትና የኢህወደግ መንግሥት የስለላ መዋቅር በሕዝቡ ያስከተሉዋቸው የደሕንነት ከፍተኛ ውጥረት፣ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማነቆዎች፣ የዋጋ ውድነትና ንረት ናቸው። መንግሥት ከአራት ኣመታት በፊት ባወጣው የገበያ ጣርያ ዋጋ ጥናት (Price Index) መሠረት በትግራይ ከተቀረው የኣገሪቱ ክፍል እጅግ የላቀ እንደነበር ነው። እነኝህ ችግሮች ሁሉም ባይሆኑም ለተቀረው የኢትዮጵያ ክፍልና ህዝብ እንግዳ ነገር ኣይደሉም።

በኔ ግምት በኢትዮጵያ የሰላማዊ ዲሞክራስያዊ ትግል ሊሳካ የሚችለው የአስተሳሰብ መሠረታዊ ለውጥ ሲኖር ብቻ ነው። የአስተሳሰብ ለውጥ ከፋፋይ የብሄረሰብ ፖለቲካ ከየትኛውም ኣቅጣጫ ይምጣ፣ በግልፅ ማውገዝን ይጠይቃል። ኣንድ ድርጅት ትግሉን ሲጀምር ይህ የመጀመርያው ኣጀንዳ መሆን ይኖርበታል። ላገር የሚቆረቆር ዜጋም ይሁን ድርጅት የሚጠቀምበትን ቋንቋ ጭምር ማስተካከልን ይጠይቃል። ከፋፋይ ቃላትን ከቋንቋው መጣል ያስፈልገዋል። በኣወንታ የሚታየው የኣንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ድርጅት ድረገፅ ለመጀመርያ ጊዜ ሰሞኑን ተዘዋውሬ ያጣሁት ቁምነገር ከፋፋይ ፖለቲካን በግልፅ በማውገዝ የህዝብን ኣንድነትና ውህደት የሚጠይቅ የድርጅቱ የኣቋም መመርያ ነው። ይልቁንም የግለሰቦችና የኣንድኣንድ ድርጅቶች ፕሮፓጋንዳ መለጠፍያ ሰሌዳ ሆኖ ነው ያገኘሁት።

እስከዛው ኢህወደግን በዘልማድ በከንቱ እየረገሙ መኖር ቢቀር ምናለ? ኢህወደግ እራሱ በቁመናው ችግር ኣይደለም፤ በህብረተሰቡ ከፋፋይ የብሄረሰብ ፖለቲካ ውስብስብ ሳብያ መፍትሄ ያጣ የፖለቲካ ስርዓት ቀውስ እንጂ።